# ***ቃለ አጋኖ ፖለቲካ***

ሊያስቅ ይችላል፡፡ የሀገር ጉዳይ ከሆነ ደግሞ ያስለቅሳል፡፡ ቃለ አጋኖ በተለይ መረን ሲለቅ ከተጨባጩ ሁኔታ ጋር መለያየትን-- መጣላትን ያመለክታል፡፡ መንስዔው ደግሞ ከዝቅተኝነት ስሜት ሊመጣ ሲችል በሌላ ጎኑ ደግሞ ራስን ተራራ ለማሳከል ከመጣር ወይ ከዳሽን አከል የጉራ በሽታም ሊወለድ ይችላል፡፡ ይህ ጉራና ዝቅተኝነት ስሜት እርስ በርስ ይመጋገባሉ፡፡ ፈረንጆቹ በደፈናው ሀይፐርቦል ሲሉት በቀልድ ደረጃ ጉዳቱ እምብዛም ነው፡፡ በስነ ፅሁፍ ግን ተዉት አትጠቀሙበት ሲሉ የአማርኛ መምህሮች አስተምረውናል፡፡ ሰማይ ብራና ቢሆን፤ ውቅያኖሶች ቀለም ቢሆኑ፤የዓለም ዛፎች ተቆርጠው መፃፊያ ቀርቅሀ ቢቀረፅና የማቱሳላ ዕድሜ ዕጥፍ ቢኖረኝ ስለ ቁንጅናሽ ፅፌ አልጨረስም ዓይነቱን ማለት ነው፡፡ ቃለ አጋኖ! ሰውየው አሮጌ ነው፤ ሽማግሌ ነው ለማለት የውጫሌን ውል ያሳሳተው፤ ባህር ዛፍ ለመጀመሪያ ጊዜ ከአውስትራሊያ ሲመጣ እንግሊዝኛ ያስተረጎመው እሱ ነው እንደማለት፡፡ ወፍራምነቱን ለመግለፅ ልብስ ሲያሰፋ ልብስ ሰፊው ሜትሩን ይዞ ብስኪሌት እየነዳ ይዞረዋል እንደማለት፡፡ በቀን ሚሊዮን ጊዜ አስብሻለሁ፤ በጣም ከመደህየቱ የተነሳ የሰፈር ጉንዳኖች ከወፍጮ ቤት እህል ያመላልሱለት ነበር እንደማለት፡፡ በቀልድ ደረጃ ፈገግ ሊያሰኝ ይቸላል፡፡

ታዲያ በፖለቲካው መስክ ይህን የመሰለው ቃለ አጋኖ ሲበረክትና ቁም ነገር መሰሎ ሲቀርብ ነገሮችን ውል ያሳጣና ከበድ ያለ መደናገርን ያስከትላል፡፡ ሀቁ ተሸፍኖ ውሸቱ የሀቅን ጠረን ብቻ ይዞ ይፈረጥጥና የበላይነትን ይይዛል፡፡ ብዙ የአፍሪካ መሪዎች ሕዝብ እንደሚጠላቸው ስለሚያውቁ፤ ምንኛ ከበርን ብለው በመርቼዲስና ሮልስ ሮይስ መኪና ቢጓዙ በመሰረቱ የልመና መንግስትን ይዘው ድሀ ሕዝብ ላይ የተሰየሙና ህዝብም የሚጠላቸው መሆኑን ያውቃሉ፡፡ በመንገድ በወታደር ታጅቤ ስከንፍ ሰው አይየኝ ባዩ መለስ ዜናዊ አንድ ምሳሌ ነው፡፡ መጠላቱንና ሌባ ና ነፍሰ ገዳይ መባሉን ያውቀዋል፡፡ ታዲያ ይህ ሁኔታ በመሪዎቹ ዘንድ የዝቅተኝነት ስሜት ይፈጥርባቸዋል፡፡ ሕዝብንም ይበልጥ እየጠሉ ይባስ ይበድሉታል፡፡ ይጨክናሉ፡፡ ራሴን በራሴ ካለንቆላጰስኩት ይሆንባቸውና ራሳቸውን ይክባሉ፡፡ የሀገሪቷ ሁለተኛው ፀሀይ፤ ፀሀዩ ንጉስ፤ ዋናው ተዋጊ፤ የሚያስፈራው አዋጊ፤ የብልሀት መደብር፤ የዕውቀት ቋት፤ የነፃነት ሀዋርያ፤ የብረት ምሰሶ፤ ዕፁብ ድንቅ አርአያ፤ የሕዝብ ዋና መምህር፤ የፅናት ባንክ፤ የሀገር ተዓምር፤ ብረት ለበስ መሪ፤ ቁጥር አንድ አውራ ዶሮ፤ ወዘተና ሌላም የአፍሪካ መሪዎች መጠሪያ ሆነው ቆይተዋል፡፡ ከኢዲ አሚን እስከ ቦካሳ እስከ “በትምህርቴ እንኳን ኤኮኖሚስት ነኝ” ባዩ መንግስቱ ወዘተ ሁሉም ለቀው--ወፈፍ አድርጓቸው ነበር፡፡ ራሱን አፄ ብሎ የነበረው ቦካሳ ለምሳሌ ለራሱ የሰጠውን ሜዳሊያ ክምር ለማሳየት በመከከለኛ አፍሪካ ክፉ ፀሐይ ረጅም ካፖርታ ያደርግ ነበር፡፡ ጉራ፡፡ ይህ በሽታ ወያኔን እንደሚያጠቃው ታዝበናል፡፡ ተተችቷልም፡፡ ግን የሰዎቹ በሽታ ተቃዋሚ ነን የሚሉትንም መልከፉ ደግሞ የማይካድ ሆኖ ይገኛል፡፡

ከቀልድና ቧልት ዓለም ውጪ ቃለ አጋኖ በፖለቲካ ውጤቱ አያምርም፡፡ በተለይም አውሪዎቹ ወይም ተናጋሪዎቹ ራሳቸው የሚሉትን ማመን ከጀመሩ! ግብዝ አምባገነኖች (ለመሆኑ ሌላ ዓይነት አለ?) የራሳቸው ቅጥረኞችና አጎብጓቢዎች የሚሏቸውን ተመልሰው አምነው ያብጣሉ፡፡ ቃለ አጋኖ በፖለቲካ መስክ ሲመጣ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ደግሞ ሌሎችን በማንቋሸሽ ላይ ያተኮረ በመሆኑ መርዙ አጥፊ ነው፡፡ ቃለ አጋኖው በአዎንታዊም በአሉታዊም ይከሰታል፡፡ ጠላት የተባለው ላይ የሚወርደው መርገም ለከት ያጣል፡፡ በዘመነ ደርግ ለምሳሌ ዝ ብ ለመቆሙ ሳይቀር ኢሕአፓ ሲወገዝ ነበር፡፡ ዛሬ ከሰላሳ ዓመት በህዋላም ቢሆን ኢሕአፓን በተመለከት በሬ መንታ ወለደ ሰፍኖ ያለ ነው፡፡ ወርቅ በእሳት ይፈተናል የሚለው ተዘንግቶ መዳብ ይቅርና ቆሮቆሮውን የሳውዲው ሼክና የወያኔ ደጋፊ ከሻኪሶ እየዘረፈ ካለው ወርቅ ጋር ሊያመሳስሉ የሚጥሩት የፖለቲካውን መስክ ሰካራም የሰራው አጥር አስመሰለውታል፡፡ ከወደ ምላሱ ፈጠን ያለውና በሺ ቃላት ምንም ቁም ነገርን ያለመናገርን ጠንቅቆ ያወቀውን ጎረምሳ ለይስሙላ ለወር ቢታሰር 27 ዓመት ከታሰረው የፖለቲካ ሰውና ፅኑ ታጋይ ኔልሰን ማንዴላ አነፃፅረው የኢትዮጵያ ማንዴላ አሉት፡፡ ለመሆኑ ሀገሪቷ የራሷ ጀግኖችና አርአያ ሊሆኑ የሚችሉ ጠፍተው ነው ደቡብ አፍሪካ ድረስ ፍለጋ የተኬደው? አንድን ሌላ የድርጅት መሪ ደግሞ በአፍሪካ ቀንድ መፅሂት (ሀገር ቤት ይታተም በነበረ ) ኢየሱሰ ክርሰቶስ፤ ማንዴላና ጋንዲን ያዋሀዱ ናቸው ተብሎ ተፅፎ የተወሰኑ አንባቢዎች በጊዜው ጉድ በዛ ብለው ተቃውሞ መፃፋቸው የሚታወስ ነው፡፡ ፖለቲካ ማለት ቅጥፈትና ውሸት ማለት ነው ብለው የሚወስዱ ሁሉ በዚህ ዓይነቱ ሁኔታ የሚጨነቁ ወይም የሚያፍሩ አይደሉም፡፡ ለመመረጥ ከፈለግክ ለህዝብ ዋሽለት

ይላሉ አሜሪካዊ ፖለቲከኞች። ታዲያ ይህ የተሳሳተ አቅዋምም ቢሆን ቢያንስ ከእውነት ትንሽም ጠረንን ይዞ የውሸትን “ሽቶ” መርጨትን ይጠይቃል እንጂ ሰማይ ላይ ምጣድ ጥጄ የባለሙያ እንጀራ ጋገርኩን አውሩና አሳምኑ የሚል አይደለም። የለከት ያለህ!

ባለፈው ሰሞን ቃለ አጋኖ ፖለቲካ ሰማየ ሰማያታን ነክቶ ሳይውል ሳያደር መንኮታኮት ተገዷል። የዛሬ 40 ዓመት የኢትዮጵያን ህዝብ መብትና ስብዕና ለማስከበር ትግል ሲነሳሳ የምድር ጣዖቶችን አውግዞ መነሳቱ ዛሬ ተቀልብሶ ስዩመ እግዚአብሔር ነኝ ያሉት አፄም በህይወት ባይኖሩም የዴሞክራሲ ጠበቃና ተሟጋች ነን ያሉት ደግሞ እንደ አፄው ሰውን ሲያሰግዱ ለማየት ተገደናል። በበኩሌ በተለይ የማስታውሰው አሳፋሪ ሰጋጅ አፄው በእነ ጄኔራል መንግስቱ ንዋይ የተሞከረባቸው መፈንቅለ መንግስት ከሽፎ ከብራዚል ሲመለሱና አዲስ አባበ ሲገቡ እግራቸው ላይ የተደፋው የሰሜን ቢትወደድ ነበር። አሳፋሪ! የነበረው ስርዓት አንዱን መለኮታዊ ስልጣን ሰጥቶ ሌላውን አፈር ያለበሰና ያዋረደ ስለነበር ከህይማኖት መስክ ውጪ የሰው ልጅ ለሰው ልጅ መስገድና ጫማ መሳም የለበትም ብለን ያመፅነውና ያንን አሳፋሪ ስርዓት ለመጣል የታገልነው ሁሉ ዛሬ ሞተን ሳናልቅ ያውም በአሜሪካ አይሮፕላን ጣቢያ ነቃን አወቅን ያሉ ዜጎች ተዘርረው የሴትየዋን ጫማ ሲስሙ ማየቱ ቢያስቀቀን የሚፈረድብን አይሆንም። ሀይማኖት ነው ፖለቲካ? ሀይማኖት ከተባለሳ ለሰው መስገድን የሚሰብከው ሀይማኖት የሴትየዋ ነው የማን? ይህ አስገርሞን ሳያበቃ ደግሞ ከወያኔ ጋር አሁንም ዕርቅ እንሻለን ባይዋን ወይዘሪት ደግሞ ሌላው ወናፍ ወይዘሮ ነፃነት /ሌዲ ሊበርቲ/ ብሎ ሲሰይማት ማንበብ ተገድድን። አንድን ሰው ነፃነት ብሎ ለመሰየም /ተራ ስም ከማውጣት ባሻገር/ ለመሆኑ መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች የሉም? የሀገር ጀግና ከማለት በፊትስ ቢያንስ የትላንት ታሪከን መቃኘት አይገባም? የዕሮብ ነፍስ ገዳይ የእሁድ ፃድቅ ሊባል ይገባል? ከ 25 ዓመት በላይ ታግለው፣ ከ 15 ዓመት በላይ ታስረው ዛሬም ያልተፈቱ እያሉ ዓመት የታሰሩ የጀግና ጀግና ሊባሉ ይገባል? የተፈቱ ሲሞገሱ መስዋዕት የሆኑትስ? ዛሬም በእስር የሚማቅቁትስ? ታሪካቸው የወንጀልና የክህደት የነበረ ዛሬ በምን ተዓምር ነው ህዝብ ያሞግሳቸው ተብሎ የሚለፈፈው? ነገ ክህደቱዎች ቢፈረጥጡ የህዝብ ወገን ሊባሉ ነው? ዶክተር ታዬ ወልደ ሰማያት ሳይጠራ ሳይጋበዝ እነ ገብሩ አስራት በመስቀል አደባባይ በተቃዋሚ ሀይሎች ስብሰባ ላይ  እንዲናገሩ መደረጉ በቂ ስህተት አልነበረምን? ስዬ አብርሀ በምን መለኪያ ነው የኢትዮጵያ ህዘብ ጀግና የሚባለው? በአሜሪካ ደለስ አይሮፕላን ጣቢያ የተካሄደውን መስተንግዶ በተመለከተ ለቁጥር የሚያታክት ሰው ተገኝቶ ነበር መባሉስ ሌላ ቃለ አጋኖ አይደለምን? በዚያውስ ኤንጂነር ሀይሉን የተቀበላቸው በመቶ ይቆጠራል መባሉና ለማሳነስ ለማንኳሰስ መጣሩ ምን ያመለክታል?

በበኩሌ ድርጅት ረቆና ተኖ መንፈስ ሲባል ጀምሮ የቀፈፈኝ ጉዳይ በመሆኑ ዛሬ ልዩ መንፈስ ውስጥ አልገባሁም። ድርጅቶች ገነን ሲሉ የሚይዙት የሚጨብጡት ማጣታቸው የተለመደ ነው። በኢሕአፓም ተመክሮ ቢሆን በጩኸቱ የቀደሙት በትግሉ ሊፀኑ የ  ሉት አይደሉም። እምነትና ፅናት የሚጠይቁት ሌላ ጠባይና ሁኔታን ነው። ጎህ ሊቀድ ሲል፣ ነፃ አውጪ ጦሩ እንጦጦ ሲደርስ ታጋዩ ከመ አሸን እንደሚፈላ ደግሞ ለማወቅ ነቢይነትን አይጠይቅም። የድል አጥቢያ አርበኛ እንደሚሉ። ድርጅቶችም ብቅ ሲሉና በለስ ሲቀናቸው አባል ነን ደጋፊ ነን ባዩ ብዙ ነው። መረር ያለው ሁኔታ ሲከሰት ግን ማን ይቆያል፣ማን ይፀናል፣ ማን ይበተናል፣ ማን ግን ቃል ኪዳኑን አክብሮ ይገኛል ነው መፈተኛው። በፖለቲካው መድረክ ስንዴና እንክርዳዱን፣ አስመሳዩንና ሀቀኛውን፣ ድንገተኛ ጨኅኚቱንና የሀቅ ታጋዩን ለይቶ ማወቅ ያሻል። ራሱን ለንዋይ የሸጠው፣ የባዕዱ ቅጥረኛ፣ ትግል አኮላሺውና የግል ጥቅም አሳዳጁ ታጋይ ወይ የህዝብ መሪ ሊባል አይገባውም። ቆራጥ የተባለው ሊቀመንበር ወደ ሀራሬ ነው የፈረጠጠው። ቆራጡ ማንዴላ የተባለው ወጠጤ ለተራ ወያኔ ነው የተጎነበሰው። ዶክተር ተብዬዎቹ ተያይዘው የፖለቲካ መሀይም ከመሆን ሌላ በባዕድ አጋፋሪነት የህዝብን አድማ ሲያከሽፉም አይተናል። ሱናሚ የተባለውን ደረቅ ምንጭ አድርገውታል። ያ ከመሪዎቹ የሚጠበቅ ወኔ ሆድ ከሀገር ሰፋና መና ሲቀር አይተናል። ከፎቅ ተወርውሮ መሰዋቱ ይቅርና የዓመት እስርም የማትቻል ሆና ምህረት ጥየቃው ላይበቃ ዳግም ለጠላት ለመስገድ አሳፋሪ ተልዕኮን ለማሟላት ሰበር ሰካው ደርቷል። ጠላትን እናጥቃ በተባለ ቁጥር በአሲምባ ወኔ ሲከዳቸው የታዩት፣ ከወያኔ ጋር ሲተቃቀፉ የባጁት፣ ትግል መረር ሲል ወገቤን ሲሉ ቆይተው የመፅሀፍ ጀግና የሚሆኑት፣ ባለፉት ዓመታት ለፋሺስት አድረው እባክዎ ጥለውን አይሂዱ ብለው ፈርጣጩን ኮለኔል ሲማጠኑ የነበሩት፣ በአጭሩ የታሪክ አተላዎች ዛሬ በቃለ አጋኖ ፖለቲካ መሪና አርአያ ሲባሉ ለመስማት መድረሳችን ያለውን ችግር የሚጠቁም ነው። ጋኖች አለቁና ምንቸቶች ጋን ሆኑ ከተባለው በባሰ ነው። ለመሆኑ ጋን ምንድነው እየተባለም ነው!

ማቹ የዩጋንዳ መሪ ኢዲ አሚን ከፈጣሪዬ ጋር የቀጥታ ግንኙነት አለኝ ይል በነበረው ዓይነት የእኛም ፖለቲከኞች እንደ አዬው ወይ ስዩመ መለኮት ነን ካላሉ በስተቀር ሰው ይስገድልን፤ ማንም አይናገረን ሲሉ ዝም ልንል አይጠበቅም፡፡ የፖለቲካ መሪዎች ጣዖቶች ሊሆኑብን አይችሉም፤ ልንፈቅድላቸውም አይገባም፡፡ የፖለቲካ ድርጅቶች ሆኑ መሪዎቻቸው በመሰረቱ ተጠሪነታቸው ለህዝብ እንጂ ለሌላ ባለመሆኑ የክብረ  ነክ ክስ ተነስቶ የመናገር መብታችን ሊታፈን አይገባም፤አይችልምም፡፡ ዕድል ከሰጡን ደግሞ ቃለ አጋኖውንም መማር እንችላለን፡፡ ታሪክን ልንረሳላቸው ማለት ነው፡፡ በህሊናችንና በአዕምሮዓችን ልንተኛበት፡፡ ስልጠናው አድካሚ አይደለም፡፡ ሀቁን ማወቅንም አይጠይቅም፡፡ በተፃራሪው ሀቅን ማሽቀንጠርን ነው የሚፈልግብን፡፡ መዋሸት ደግሞ ከባድ አይደለም፡፡ የቅፅል መዝገበ ቃላትም ቢሆን ሞልቷል፡፡ ሳይቀሱ መምሬነትም አያሰቸግርም፡፡ ሳይታገል ጣይ፤ሳይወጋ ገዳይ ደግሞ ሞልቷል፡፡ ሽንፈትን ድል ብሎ መዝፈን ደግሞ ወያኔም ጫካ ሳለ ያሳየው ነው፡፡ የከዳ ወኔን ሌለን በመክሰስ መሸፋፈንም ከተከሰተ ውሎ አድሯል፡፡ ታዲያ ቃለ አጋኖውን ማስተጋባቱ ምን ያቅታል? ቪቫ መንግስቱ? ቪቫ መለስ? ቪቫ ወዘተ ..... ጣቶች መቀሰሩም ሆነ ግራ እጅ ማንሳቱ ዋጋ ካላስከፈለ--ጉዳት ካላመጣ-- እጅ ያለው ሁሉ ሊያደርገው የሚችል ነው፡፡ ሀገር ተንቃ፤የሀገር የሆነው ሁሉ ርካሽ ተብሎ፤ ሰብዕና ለባዕድ ተሸጦ፤ ህዝብ ተረስቶ ባዕድ በሀገር ላይ ወሳኝ ተደርጎ በተወሰደበት ሁኔታ ቃለ አጋኖ ራሱ ቋንቋና ቃና ቢቀይር የሚያስገርም አይሆንም፡፡ በባዕዳን ኤምባሲ ተኮልኩሎ ልመና ማካሄዱ ማሳፈሩ ቀርቶ ንቃት ብልህነት ተብሏልና ነው፡፡ አይረቢትን ካረቧት ጊዜ አልፏል፡፡

ሀገር ሸቀጥ አይደለችም በሚለው የሚያምኑ ሁሉ፤ ለሀገር እንታገል ሲሉ ለራሳችን ስልጣንና ዝ እንዋደቅ የማይሉ ከሆኑ፤ ትዕዛዝ የሚቀበሉት ከሕዝብ እንጂ ከባለዶላር ፈረንጅ እስካልሆነ ድረስ ቃለ አጋኖ ፖለቲካን ፊት የሚሰጡ አይሆኑም፡፡ ነገሮችን በልክ መያዝ አለመቻሉ የሚከሰቱ ቅራኔዎችንም ቢሆን በተገቢው መንገድ ማስተናገድን ያደናቅፋል፡፡ ሰርጎ ገቦችና ከፋፋዮች አስረሽ ምቺው የሚሉበት ሁኔታን ያገኙና አንዱን የደገፉ መስለው ሌላውን አክርረው በማውገዝ ብጥብጥን ያሰፍናሉ፡፡ ማን በዚህ እንደሚጠቀም ማወቅ ደግሞ አያስቸግርም፡፡ የአንድን ሰው ማርጀት ለመግለፅ ለማቱሳላ ጋር ገበጣ ይጫወት ነበር ማለቱ አያስፈልግም፡፡ የፖለቲካ መሪ የተባሉትንም ጊዜ ወሰዶና ፈትኖ ማየት እንጂ ጎህ ሳይቀድ ጋንዲም ማንዴላም ናቸው፤ ወይዘሪት ነፃነት ናት፤ የሀራችን ሁለተኛ ፀሐይ ነው ወዘተ ማለቱ ምንም ጠቀሜታ የለውም፡፡ በተለይ ሳይውል ሳያድር ደግሞ ጥምብ እርኩሳቸውን ወደ ማውጣቱ የምንሰማራ ከሆነ፡፡ አደብ! ለከት! የቀባጣሪ አፍ ጠማማ ነው እንዳንባል፡፡

ይህን በመፃፌ ሊከተል የሚችለውን ቃለ አጋኖ ውግዘት መገመቴ አልቀረም፡፡ ማን ይፈራል ሞት ብሎ ከዘመረና ሞትንም ከተጋፈጠ ትውልድ ጋር የታገልኩ በመሆኔ እውነቱን ተናግሮ የመሸበት ያድሯል ባይ ነኝ፡፡ ፖለቲካችን መልክ እንዲይዝ፤ ትግላችን እንዲጠናከር ከተፈለገ የቃለ አጋኖ ፖለቲካና ፕሮፓጋንዳ አባወራዎችን ዝም ማሰኘት ወይም ከመድረክ ማግለል ያስፈልገናል፡፡ ትሁት ሆነን፤ልካችንን አውቀን፤ ሀቀኛውን ከአስማሳዩ ለይተን፤ ጅግናና የወረቀት ነብሩን አበራይተን፤ የወያኔን ሰርጎ ገቦች አሳፍረን፤ ቃለ አጋኖ ደፋቂዎችን ዝም አሰኝተን፤ ሀቀኛ ሀገር ወዳዶችን አቀራርበንና አስተባብረን፤መረቅ መንፈሰ መሆኑን ትተን፤ ከህዝብ ተመሳስለንና አጉል መርጥ በሉኝን አስወገደንና ከሁሉም በላይ ደግሞ ለባዕድ ሆነ ለህገረ በቀሉ መስገድን ጫማ መሳምን ወገድ ብለን፤አንገት ቀና ፤ራስ ቀና፤ልብን ደንደን ሞላ አድርገን ታሪካችን በሰጠን ተመክሮ መሰረት መታገልና የሽፍጥና የመጎንበስ ሳይሆን የጀግንነት ታሪክ መፃፍ መቻል አለብን፡፡ አለበለዚያማ ሚሊዮን ጊዜ ያህያ ባል ከጅብ አያስጥልም ይባልብናል፡፡ ቃለ አጋኖ!!!